## ጋ ዜ ጣ ዊ   መ ግ ለ ጫ

# በኢትዮጵያ ስለ ተፈጸመው የፋሺሽት የጦር ወንጀል ዓለም አቀፍ ተቃውሞ

የካቲት 12 ቀን 2005 ዓ/ም (February 19, 2013) በዓለም አቀፍ ደረጃ በ30 ከተሞች በሚከናወኑት የተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፎችና ስብሰባዎች በአዲስ አበባ ከተማ፤ በየካቲት 1929 ዓ/ም የተጨፈጨፉት 30000 ኢትዮጵያውያንና፤ በቫቲካን ድጋፍ የኢጣልያ ፋሺሽቶች ከ1928-33 ዓ/ም ስለ ፈጸሙት የጦር ወንጀል ይታሰባል።

## የፋሺሽት ጦር ወንጀሎች በኢትዮጵያ፤

በኢትዮጵያ የተፈጸሙት የኢጣልያ የጦር ወንጀሎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ከባድ ጥፋቶች አስከትለው ነበር፤

1. በዓለም አቀፍ ሕግ በተከለከለ በብዙ የኢጣልያ አውሮፕላኖች በተነሰነሰ የመርዝ ጋዝና በሌላም የጦር መሣሪያዎች በመጠቀም አንድ ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን ተጨፍጭፈዋል፤
2. 2 000 ቤተ ክርስቲያኖችና 525 000 ቤቶች ተደምስሰዋል፤
3. 14 ሚሊዮን እንስሳትን ጭምር ያወደመ የአካባቢ ብክለት ተከስቷል።

በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ፤ እንደሚባለው፤ የኢጣልያ መንግሥት በቅርቡ አፊሌ በምትሰኝ ከሮም ከተማ ወደ ደቡብ በምትገኝ ሥፍራ፤ ለፋሺሽቱ የጦር ወንጀለኛ ለሮዶልፎ ግራዚያኒ አንድ መካነ መቃብርና መናፈሻ አቋቁሞለታል። እ.ኤ.አ. በ1947 ኢጣልያ ለኢትዮጵያ የከፈለችው 6 ሚሊዮን ስተርሊንግ ፓውንድ ካሣ፤ ፍጹም የማይመጥን፤ ሌላው ኢፍትሐዊ ድርጊት ነው።

| | |
|---|---|
|  |  |
| በፋሺሽቶች የተሰቀሉ የኢትዮጵያ አርበኞች | የኢጣልያ ፋሺሽቶች ከቆረጡት የኢትዮጵያዊ አርበኛ ራስ ጋር ሲታዩ |

**<u>ቫቲካን ለፋሺሽቶች ያበረከተችው ድጋፍ፤</u>**

በጊዜው በፖፕ ፓየስ 11ኛ፤ ቀጥሎ በፖፕ ፓየስ 12ኛ ትመራ የነበረችው ቫቲካን በፋሺሽቱ የጦር ወንጀል ሙሉ በሙሉ ተሳታፊ ነበረች። ይህንንም ከሚያረጋግጡ ብዙ ማስረጃዎች ውስጥ የሚከተሉትን መመልከት ይቻላል፤

## 1ኛ/<u>ታዋቂው "ኒው ዮርክ ታይምስ" (New York Times) ጋዜጣ</u>፤

ይህ በዓለም-አቀፍ ደረጃ ታዋቂና ታማኝነት ያለው ጋዜጣ፤ የካቲት 6 ቀን 1929 ዓ/ም (February 13, 1937) ስለ ፖፕ ፓየስ 11ኛ ባወጣው ዜና ከዚህ እንደሚከተለው ዘግቧል፤

> "Earlier today the Pontiff had given his recognition of Italian sovereignty over Ethiopia by bestowing his apostolic benediction upon Victor Emmanuel as "King Of Italy and Emperor of Ethiopia." (ትርጉም፤ ቀደም ሲል ዛሬ አቡኑ "ለኢጣልያ ንጉሥና የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት"፤ ለቪክቶር ኢማኑኤል፤ ቅዱስ ቡራኬያቸውን በመስጠት ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ ስላላት ሉዓላዊነት እውቅናቸውን ገልጸዋል።) ሙሉውን ዘገባ ከዚህ በታች ካለው መመልከት ይቻላል፤
>
> http://www.globalallianceforethiopia.org/piusxi.pdf

## 2ኛ/ ማንቸስተር ጋርዲያን (Manchester Guardian)

የካቲት 5 ቀን 1922 ዓ/ም (February 12, 1929) በወጣው በዚህ ጋዜጣ ዘገባ የሚከተለው ጽሑፍ ይነበባል፤

> "Pope Pius XI is credited with much admiration for Mussolini. That the Italian clergy as a whole are pro-Fascist is easy to understand, seeing that Fascism is a nationalist, authoritarian, anti-liberal, and anti-Socialist force." (ትርጉም፤ ፖፕ ፓየስ 11ኛ ለሙሶሊኒ ስላላቸው ከፍተኛ አድናቆት ይነገርላቸዋል። የፋሺሽት ሥርዓት አምባገነናዊ፤ ብሔርተኛ፤ ፀረ-ዲሞክራሲና ፀረ-ሕዝባዊ ኃይል ስለ ሆነ የኢጣልያ ካሕናት በአጠቃላይ የፋሺሽት ደጋፊ መሆናቸውን በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል።)

3ኛ/ አቭሮ ማንሐታን (Avro Manhattan) የተሰኘው ጸሐፊ፤ "The Pope in World Politics" በተሰኘው መጽሐፉ፤ የፋሺሽቱ ጦር አዲስ አበባ ሲደርስ ፖፕ ፓየስ 11ኛ የሚከተለውን የደስታ መልእክት አስተላልፈው ነበር፤

> "The triumphant joy of an entire, great and good people over a place which, it is hoped and intended, will be an effective contribution and
>
> 3
>
> prelude to the true place in Europe and the World." (ትርጉም፤ ለአውሮፓና ለዓለም መልካም ጅማሮና ሁነኛ ደረጃ ተገቢ አስተዋጽኦ እንዲሆን ለታቀደና ተስፋ ለተጣለበት ቦታ (ኢትዮጵያን ማለት ነው) የታላቅና ግሩም ሕዝብ (ኢጣልያኖችን ማለት ነው) ከፍ ያለ ደስታ።)

4ኛ/ የቱራኖ ጳጳስ በሚከተለው ገለጻ በኢትዮጵያ ላይ የተከናወነውን የፋሺሽት የጦር ወረራ ባርከው ነበር፤

> "The war against Ethiopia should be considered as a holy war, a crusade" (as Italian victory would) "open Ethiopia, a country of infidels and schismatics, to the expansion of the Catholic Faith." (ትርጉም፤ በከሐዲዎቹ ሐገር፤ በኢትዮጵያ፤ የካቶሊክን ሃይማኖት ለማስፋፋት ስለሚጠቅም በኢትዮጵያ ላይ የተፈጸመው ጦርነት እንደ ቅዱስ ጦርነት፤ መንፈሳዊ ዘመቻ መቆጠር አለበት።)



የቫቲካን ካሕን የፋሺሽቱን ጦር ሲባርኩ

**<u>ፍትሕ ለኢትዮጵያ፤</u>**

በቫቲካን ድጋፍ፤ በኢትዮጵያ ላይ ለተፈጸሙት የጦር ወንጀሎች ለኢትዮጵያ የሚያስፈልገው ፍትሕ የሚከተለው ነው፤

1ኛ/ ቫቲካን የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ እንድትጠይቅ፤
2ኛ/ የኢጣልያ መንግሥት፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ተገቢውን ካሣ እንድትከፍል፤
3ኛ/ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት፤ በኢትዮጵያ ላይ የፈጸመውን የጦር ወንጀል በመዝገቡ እንዲያውል፤
4ኛ/ የኢጣልያና የቫቲካን መንግሥቶች ይዘውት የሚገኙትን የተዘረፈ ንብረት ለኢትዮጵያ እንዲመልሱ፤
5ኛ/ የቫቲካን ተወካይ በተገኙበት፤ ከሮም ከተማ በስተደቡብ በምትገኝ አፊሌ በምትሰኝ ሥፍራ የተቋቋመውን የሮዶልፎ ግራዚያኒን መካነ መቃብርና መናፈሻ የኢጣልያን መንግሥት እንዲያፈርስ።



የቫቲካን ተወካይ በተገኙበት ለሮዶልፎ ግራዚያኒ የተቋቋመው መካነ መቃብር ሲመረቅ

ለተጨማሪ ማስረጃ፤
Global Alliance for Justice – The Ethiopian Cause
4002 Blacksmith Drive, Garland, TX 75044, USA
Tel: (214)703 9022; Email: info@globalallianceforethiopia.com
http://www.globalallianceforethiopia.org

አባሪ ፩ ፡ የሚካፈሉ ከተሞች ዝርዝር

| | |
|---|---|
| 1 | ዋሺንግቶን ዲሲ |
| 2 | ኒው ዮርክ |
| 3 | ዳላስ ፎርት ዎርዝ |
| 4 | አትላንታ |
| 5 | ሳን ሆሴ |
| 6 | ሲያትል |
| 7 | ላስ ቬጋስ |
| 8 | ሎስ ኣንጀለስ |
| 9 | ዴንቨር |
| 10 | ሁውስቶን |
| 11 | ቺካጎ |
| 12 | ቦስቶን |
| 13 | ዴትሮይት |
| 14 | ፊላደልፊያ |
| 15 | ሚያሚ |
| 16 | ታምፓ |
| 17 | ቶሮንቶ |
| 18 | ሎንዶን |
| 19 | ስቶኮልም |
| 20 | ሮም |
| 21 | ጄነቫ |
| 22 | ብራስልስ |
| 23 | በርሊን |
| 24 | ፍራንክፈርት |
| 25 | አምስተርዳም |
| 26 | ሞስኮ |
| 27 | ጀሩሳሌም |
| 28 | ሲድኒ |
| 29 | ጆሃንሱቡርግ |
| 30 | ናይሮቢ |
| 31 | ካምፓላ |
| 32 | ኪንግስቶን |
| 33 | ሉሳካ |
| 34 | አውስትራሊያ |
| 35 | ቶክዮ |
| 36 | ጀሩሳሌም |
| 37 | ኣዲስ አባባ |
| 38 | ዋሺንግቶን ዲሲ |